ታህሳስ3/2004 ዓ.ም.

# መኢአድን ለማጥፋት ገዥው ፓርቲ እየፈጸመ ያለውን ደባ አስመልክቶ መኢአድ ወይይት አካሄደ

***በውጭ ሃገር የሚገኙ ድጋፍ ሰጭ ማነበራትና ዞኖች በስብሰባው ላይ አስተያየት ሰጥተዋል፡፡***

የገዥው ፓርቲ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅትን (መኢአድ) ለማጥፋት እየፈፀመ ያለውን ደባዎች አስመልክቶ የመኢአድ ከፍተኛ አመራሮች ከአባላቱ ጋር አዲስ አበባ በሚገኘው የፓርቲው ዋና ጽ/ቤት ታህሳስ 1/2004 ዓ.ም ሰፊ ወይይት አካሄዱ፡፡ በመፍትሔ ሃሳቦችም ላይ ተወያይተዋል፡፡ በዕለቱ በተካሄደው ስብሰባ ላይም የሰሜን አሜሪካ፣ የካናዳ እና የአወሮፓ ድጋፍ ሰጭዎች፣ እንዲሁም ከደቡብ፣ ከምሥራቅና ከሰሜን ኢትዮጵያ የተወሰኑ የፓርቲው የዞን አመራር አባላት በጉዳዩ ላይ አስተያየታቸውን በቴሌ ኮንፈረንስ ሰጥተዋል፡፡

በዕለቱ በተካሄደው የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት ስብሰባ ላይ አቶ ወንድማገኝ ደነቀ የፓርቲው ተቀዳሚ ምክትል ሊቀመንበር፣ አቶ ተስፋዬ ታሪኩ ዋና ጸሃፊ እና አቶ አዳሙ ተሰማ የአስተዳደርና ፋይናንስ ኃላፊ በድርጅቱ ሠርገው የገቡ የኢሃዲግ ተላላኪዎች እየፈጸሙ ያሉትን ሴራ በዝርዝር ለተሰብሳቢዎች አቅርበዋል፡፡ በዚህ መሠረትም በአቶ ማህተመ በኩረና በአቶ አሰፋ ሃብተወልድ እየተመራ ያለው የሰርጎ ገቦች ቡድን እየፈጠረ ያለውን ፓርቲውን የማወክ እንቅስቃሴዎች ከጅምሩ አንስቶ አሁን እስካለበት ደረጃ አብራርተዋል፡፡

አቶ ተስፋዬ ታሪኩ ገዥው ፓርቲ ጠንካራና ህዝባዊ መሠረት ያለውን መኢአድን ለማጥፋት ላለፉት ሃያ ዓመታት በቀጥታ በፓርቲው መሪዎች፣ በአባላቱና በደጋፊዎቹ ላይ የሚፈጽማቸው አሰብአዊ ድርጊቶች እጅግ አስከፊ መሆናቸውን ጠቅሰው <u>በአሁኑ ወቅት ደግሞ በጥቅም የታወሩ ሠርጎ ገብ ተላላኪዎችን በማጠቀም መኢአድን የወያኔ ኢህአዴግ ተለጣፊ ለማድረግ እንደፈለገው በሚዘወው ምርጫ ቦርድ አማካኝነት እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡</u> ማዕከላዊ ኮሚቴው ሃምሌ 30/2003 ዓ.ም. ጉባዔውን ሲያካድ የእነአቶ ማህተመ በኩረ ሰርጎ ገብ ቡድን ዋና ጸሃፊው ሲቪል በለበሱ በሁለት የደህንነት አባላት እንዲታሠሩ ያደረጉትን ተንኮል ጠቅሰዋል፡፡ የፓርቲው የመተዳደሪያ ደንብን የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው የማስተካከል ሥራ በሚያከናወንበት ወቅት በታች የሆኑት እነዚህ ሠርጎ ገቦች ለእነሱ በሚመች መልክ ለመቅረጽ ሲያደርጉ የነበረውን ግብ ግብና በኋላም ላይ ሰነዱን ለምርጫ ቦርድ ለማስገባት በሚፈለግ ጊዜ አቶ ማህተም በኩረ ፊርማና ማህተም አላደርግም በማለት ለተወሰኑ ቀናት አስችግረው የነበሩ መሆናቸውንም ጨምረው ጠቅሰዋል፡፡

የወያኔ (ኢህአደግ) ሰርጎ ገብ ተላላኪዎች በሚጠቀርበር የአዲስ አበባ የመመኢአድ ምክር ቤትንና የአዲስ አበባ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትን ምርጫ በማጭለብኝነት ማካሄዳቸውንና የአዲስ አበባ አባላትም ጉዳዩን ተቃውመው ፔቲሽን ተፈራርመው ለማዕከላዊ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በማቅረባቸውና ምርጫውም ህገ ወጥ መሆኑን የማዕከላዊ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው በማንዘቡ ከደንብ ውጭ የተካሄደውን ምርጫ ማሰረዙን ጠቅሰው በቂ ዝግጅት ተካሂዶ ምርጫው በዲሞክራሲያዊ መንገድ እስከሚካሄድ ድረስ ቀደም ሲል የነበረው የአዲስ አበባ ምክር ቤት እና የአዲስ አበባ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሥራዎችን እንዲያከናወኑ መወሰኑንም ጠቁመዋል፡፡

ከበታች ቡድን አባላት ወስጥ አቶ ማነተመ በኩረ በእጃቸው የሚገኘውን ማነተም አዲስ ለተመረጡት የአስተዳደርና የፋይናንስ ኃላፊ እንዲያስረክቡ በቅድሚያ በጽሁፍ በኋላም በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባ ላይ

ሲጠየቁ አላስረከብም ለምርጫ ቦርድ ነው የሚሰጠው በማለት ስብሰባውን ረግጠው መውጣታቸውንም የመኢአድ አመራሮች ለተሰብሳቢዎቹ አስረድተዋል፡፡

የመኢአድ አመራሮች ገለፃቸውን በመቀጠልም ሰርጎ ገቦቹ መስከረም 18/2004 ዓ.ም. የፓርቲው ፕሬዚዳንት፣ ተቀዳሚ ምክትል ፕሬዚዳንት፣ ዋና ጸሃፊውና ሌሎቹም የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት በሌሉበት ለብቻቸው ኮረም ባልሞላበት ሁኔታ ተሰብስበው ፕሬዚዳንቱን ለህግና ሥነ ሥርዓት ኮሚቴ አቅርበናል፤ ዋና ጸሃፊውን አግደናል እና ሌሎችንም ውሳኔዎች አስተላልፈናል ማለታቸው ፍፁም ከደንብ ውጭ መሆኑን የመኢአድ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጾችን በመጥቀስ አብራርተዋል፡፡

በታች ከሆነው ከሠርጎ ገቦቹ ቡድን አባላት ወስጥ አቶ ጌታቸው ባያፈርስ ከመኢአድ አባልነታቸው በተጨማሪ የአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ አባል ሆነው ማገኘታቸው በማስረጃ በሚረጋገጡ በመኢአድ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ከአባልነት የሚያሰርዝ በመሆኑ የተባረሩ ግለሰብ መሆናቸው፣ አቶ አሰፋ ሃብተወልድ ፈርመው ባስገቡት ደብዳቤ ከሥራ አስፈፃሚ አባልነት እራሳቸውን ያገለሉ መሆናቸውን በማሳወቃቸው ፓርቲው ከሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባልነት ስንብት የሰጣቸው በመሆኑ፣ አቶ ማህተመ በኩረም ማህተም አላስረክብም በማለታቸው በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት የታገዱ መሆናቸው እየታወቀ እነሱ ግን አሁንም እራሳቸውን የመኢአድ አመራር አድርገው በመቁጠር አብላጫ ቁጥር ያለን እኛ ነን እያሉ መግለጫ መስጠታቸው ፍፁም ህገ ወጥነትና ማጭበርበር መሆኑን የመኢአድ አመራ አባላት ለተሰብሳቢዎቹ ገልጸዋል፡፡

በታኞቹ በተለያዩ ጊዜያት በሚያወጡት መግለጫ ላይም በሌሉ ሰዎች ስም አስመስለው እየፈረሙ አብላጫ ቁጥር አለን ማለታቸውን አቶ ተስፋዬ ታሪኩ የወ/ሮ ፀገነት ይልማን ምሳሌ በመጥቀስ አስረድተዋል፡፡ ወ/ሮ ፀገነት ይልማ ከፓርቲው አመራርነትም ሆነ ከአባልነት በራሳቸው ፈቃድ ሚለቀቂያ አቅርበው የለቀቁ መሆናቸው እየታወቀ ሰርጎ ገቡ ቡድን ግን ከእኛ ጋር ናቸው በማለት በስማቸው የሃሰት ፊርማ ፈርሞ መግለጫ አብረው እንደሰጡ አስመስሎ ማቅረቡንም ዋና ጸሃፊው ጨምረው አብራርተዋል፡፡

የመኢአድ አመራር በስብሰባው ለተገኙት የመኢአድ አባላት ሰርጎ ገቡ ቡድን የተጠቀሱትንና ሌሎችም የፈጸሟቸውን ህገወጥ ተግባራት ከዘረዘሩ በኋላ የኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድ ከአፍራሹ ቡድን ጋር ቆሞ እየፈጸመ ያለውን ደባም አጋልጠዋል፡፡

ይህንንም ሲያብራሩ ምርጫ ቦርድ በተደጋጋሚ ጊዜያት ለመኢአድ በፃፉቸው ደብዳቤዎች፣ በተለያዩ ጊዜያት በሥነ ሥርዓት ጉድለት ከፓርቲው የተባረሩና የታገዱ ሰዎችን እንዲሁም በራሳቸው ፍቃድ ፓርቲውን የለቀቁ ግለሰቦችን ያካተተ ጠቅላላ ጉባዔ እስከ ህዳር 30/2004 ዓ.ም. እንዲጠራ ማዘዙን ጠቅሰዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ፓርቲው በተሰናበቱና በታገዱ ሰዎች ምትክ የተወሰኑ ሰዎችን መተካታቸውን ምርጫ ቦርድ የማይቀበለው መሆኑን በደብዳቤ እንዳሳወቃቸውም አመራሮቹ በስብሰባው ላይ አንስተዋል፡፡ በቅርብ የተቀረጸው የፓርቲው ማህተም ሊሠራ የሚችለው እስከ ታህሳስ 30/2004 ዓ.ም ድረስ ብቻ ነው የሚል ትዕዛዝም ምርጫ ቦርድ እንዳስተላለፈላቸው ጠቅሰዋል፡፡ ምርጫ ቦርድ በመኢአድ ላይ እያስተላለፈ ያለው ትዕዛዝ ከተሻሻለው የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 573/2000 ዓ.ም. እና 2001 ዓ.ም ከጸደቀው የመኢአድ መተዳደሪያ ደንብ ጋር ፍፁም የሚፃረስ መሆኑንም ኃለፊዎቹ ገልጸዋል፡፡ ዘርዝረው ሲያብራሩም አዋጅ ቁጥር 573/2000 ዓ.ም. በአንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ <<ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የመተዳደሪያ ደንብ ይኖረዋል፡፡ >> ካለ በኋላ <<የመተዳደሪ ደንቡም፦

ረ/ በአባላት ላይ ስለሚወሰድ የሥነ ሥርዓትና የሥነ ምግባር እርምጃ፣

ሰ/ የፖለቲካ ፓርቲው የጉባዔ ስብሰባ የሚያካሂድበትን ገዜና ሁኔታ ያካተተ መሆን አለበት፤ >> እንደሚል ያስረዳሉ፡፡ ማብራሪያቸውን በመቀጠልም

አዋጅ ቁጥር 573/2000 ዓ.ም. አንቀጽ 16 << የፖለቲካ ፓርቲ በራሱ ጉዳይ ላይ ስላለው ነፃነት>> በሚል ርዕስ ሥር በንዑስ አንቀጽ 1. <<ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የፖለቲካ ፕሮግራሙና

የመተዳደሪያ ደንቡን የሚፀድቅበትንና የሚሻሻልበትን እንዲሁም ስብሰባ የሚካሄድበትን ሥነ ሥርዓት በመተዳደሪያ ደንቡ ይወስናል፡፡ >> የሚል ማስፈሩን የመኢአድ አመራሮች ጠቅሰው 2001 ዓ.ም. የጸደቀው የመኢአድ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 9. ንዑስ አንቀጽ 9.1.2. <<ጠቅላላ ጉባዔው በሁለት ዓመት አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፡፡ >> እንደሚል አወስተው መኢአድ ጠቅላላ ጉባዔዎን ካካሄደ ገና ዓመት እንኳን ሳይሞላው ምርጫ ቦርድ ጣልቃ ገብቶ እስከ ህዳር 30/2004 ዓ.ም. አካሂዱ ማለቱ ፍፁም አግባብነትነት መሆኑን የመኢአድ ኃላፊዎች ለተሰበሳቢዎች ገልጸዋል፡፡

በተጨማሪም ምርጫ ቦርድ በጉባዔው ላይ ከፓርቲው የለቀቁና የታገዱ ሰዎች ሁሉ ይገኙ ማለቱ ኢዲሞክራሲያዊ አሰራር መሆኑን ከጠቀሱ በኋላ አዋጅ ቁጥር 573/2000 ዓ.ም አንቀጽ 30 << ከአባልነት መወገድ>> በሚለው ርዕስ ሥር

1/ << አንድ የፖለቲካ ፓርቲ አባል የፖለቲካ ፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ በወሰነው መሠረት ከአባልነት ሊወገድ ይችላል፡፡ >>

2/ <<ከፖለቲካ ፓርቲ መተዳደሪያ ደንብ ወጪ ከፓርቲ አባልነት የተወገደ አባል በወሳኔው ላይ ቅሬታ ሲኖረው መወገዱ በተገለጸለት በሦስት ወር ጊዜ ወስጥ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፡፡ >> ይላል፡፡

በመኢአድ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 1 ቁጥር 11 ላይ <<ፓርቲዎን ለማዳከም፣ ለማብታተን ወይም ለማፍረስ መካራ ወይም ተጨባጭ እንቅስቃሴ ሲያደርግ በተገኘ የፓርቲ አባል ላይ ፕሬዚዳንቱ ጊዜያዊ እገዳ ይጥላል፡፡ ቀጥሎም እንደ አስፈላጊነቱ ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴና ለማዕከላዊ ምክር ቤት ወይም ለጠቅላላ ጉባዔ አቅርቦ ወሳኔ ያሰጣል፡፡ >> ማለቱን አመራሮቹ ለተሰብሳቢዎቹ ከጠቀሱ በኋላ እነ አቶ ማህተመ በኩረ የተወሰነባቸው በደንቡ መሠረት ሆኖ እያለ ምርጫ ቦርድ ለእነሱ ጥብቅና ቆሙ ከአዋጅና ከደንብ ውጭ የፓርቲዎን ነፃነት ተዳፍሮ <<ጠቅላላ ጉባዔ ጥሩ፤ የተወገዱ ሰዎች ስብሰባችሁ ላይ ይገኙ>> የሚልበት ምክንያት በፍጹም ፍትሃዊ አይደለም ብለዋል፡፡

በአዋጁ አንቀጽ 30 ቁጥር 2 ላይ ከፓርቲ አባልነት የተወገደ አባል ቅሬታ ካለው ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቤቱታ ሊያቀርብ እንደሚችል እየገለፀ እያለ እንዴት ሆኖ ነው ምርጫ ቦርድ አለድርሻው የፍርድ ቤትን ቦታ ወስዶ የሚይገባ ትዕዛዝ የሚሰጠው? በማለት የመኢአድ አመራር አባላት ወሳኔው ተገቢ ያልሆነና እጅግ አሳሳቢ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በተሰናበቱ አመራሮች ምትክ ከማዕከላዊ ምክር ቤት አባላት አራት ሰዎችን ወደከፍተኛ አመራርነት እንዲመጡ ካደረግን በኋላ አዋጅ 573/2000ዓ.ም አንቀጽ 21 ቁጥር 1 እና 2 በሚያዘው መሠረት ለምርጫ ቦርድ ስናሳወቅ ቦርዱ እወቅና ማስጠት ሲገባው ማገደም መተካትም አትችሉም ማለቱ አዋጁ ከሰጠው ኃላፊነት ውጭ በመሆኑ እንቃወማለን ብለዋል ማብራሪያ ሰጭዎቹ፡፡

አቶ ተስፋዬ ታሪኩ **ምርጫ ቦርድ እየፈጸመበን ያለው ተገቢ አለመሆኑን ጠቅሰን መጀመሪያ ለምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት፣ ቀጥሎም ለቦርዱ ሰብሳቢ ለፕሮፌሰር መርጋ በቃና ያቀረብነው አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም ካሉ በኋላ ህዳር 19/2000 ዓ.ም ቦርዱ ለፓርቲዎች ባዘጋጀው የምክክር መድረክ ላይ መኢአድ የገጠመውን ችግር እንዳያቀርብ ዕድል ተነፍጎታል ብለዋል፡፡ ከዚያ በኋላም ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት በሜድ ከፕሮፌሰር መርጋ በቃና ጋር በአካል ለመወያየት ቀጠሮ እንዲያዝልን ያደረግነው መካራም የቦርዱ ሰዎች ፈቃደኛ በለመሆናቸው ሊሳካ አልቻለም፡፡ ከዚህ በተቃራኒው ግን የታገዱትን ግለሰቦች በየጊዜው እያነጋገሩዋቸው መሆኑን መረጃ ደርሶናል ካሉ በኋላ ምን እየተጠነሰሰልን እንደሆነም ማመት ከባድ አልሆነብንም ብለዋል፡፡**

ማብራሪያወን የሰጡት የመኢአድ ከፍተኛ አመራሮች ምርጫ ቦርድ ከሚፈጽመው መኢአድን የማጥቃት እንቅስቃሴ በተጨማሪ የወያኔ/ኢህአዴግ የደህንነት ሰዎች በአባሎቻችን ላይ እየፈጠሩ ያሉት ጫና ቀላል የሚይባል ነወ፤ ብለዋል፡፡ ሁኔታወን ሲገልጹም **ሰሞኑን አንዳንድ አባሎቻችን በደህንነት ሰዎች**

**<<ኢንጂነር ኃይሉን ትታችሁ ከነማህተመ ጋር ካልሠራችሁ በህይወታችሁ ላይ ችግር ይገጥማችኋል>> ማለታቸውንና ስማቸውንም ይፋ የማድረገው ለደህንነታቸው ስንል ነው ብለዋል፡፡ ከፍተኛ ሥልጣን ያላቸው የፖሊስ ኃላፊዎችም ለአባሎቻችን ተመሳሳይ ማስፈራሪያ እያደረሱ ነው ብለዋል፡፡ የደህንነት አባል የሆኑት የአቶ ማህተመ በኩረ ወንድምም ሰሞኑን ከሥራ አጋሮቻቸው ጋር ወለቴቸው በመኢአድ ጽ/ቤት አካባቢ የሚወጣና የሚገባውን ሰው መሚልከትና የመኪና ታርጋ መመዝገብ ማሆኑንም ገልጸዋል፡፡**

የወይይቱ አቅራቢዎች ያላቸውን ስጋት ሲጠቅሱም ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲን ለአቶ አየለ ጫሚሶ፣ በዶክተር ሚራ ጉዲና የሚመራውን ኦብኮን ለመቶ አለቃ ቶለሳ ተስፋዬ እንዳስረከቡ ሁሉ መኢአድንም ለወያኔ ኢሃዴግ ተለጣፊዎች ሊሰጡ እንደሚሞክሩ ፓርቲው እየተፈጸመበት ካለው ደባ ለሚረዳት መቻላቻውን ጠቁመዋል፡፡ የመኢአድ ከፍተኛ አመራሮች ጠቅላላ ጉባዔ ጥሩ ማባላቸውን የተቃወሙበትን ምክንያት ሲያስረዱም ዋንኛው ምክንያታቸው የምርጫ ቦርድ ትዕዛዝ ከአዋጁና ከደንባችን ውጭ ፈሩን የሳተና ከሚርህም አኳያ ጤሊቃ ገብነት በማሆኑ፣ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ጠቅላላ ጉባዔ ለመጥራት የሚያስፈልገው በጀት ከፍተኛ በማሆኑ ዓመት ባልሞላው ጊዜ በታኝና አፍራሾች ሥርዓት በጣሱ ቁጥር ጠቅላላ ጉባዔ መጥራት ተገቢ ባለማሆኑ እንደሆነ አስረድተዋል፡፡ አዲስ አበባ ላይ ጥቂት አመራር አባላት ከበታኞቹ ጋር ቢቆሙም በመላው ኢትዮጵያ ከሚገኘው የመኢአድ ሚለትም የዞን፣ የክፍለ ከተሚና የወረዳ አመራሮችና አባላት ቁጥር ሲነጻጸር እነሱ ኢምንት ናቸው ብለዋል፡፡ ከየዞኑ ካሉ አመራርና አባላት የድጋፍ ደብዳቤዎች እየደረሳቸው ማሆኑንም አመራሮቹ ሚጃዎቻቸውን ለተሰብሳቢዎች በማሳየት አስረድተዋል፡፡

የመኢአድ ከፍተኛ አመራር አባላት ለኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድ ላቀረቡት ህጋዊ ጥያቄ ምላሽ በማጣታቸው **በተወካዮች ምክር ቤት ለህግና ሥነ ሥርዓት ኮሚቴ ደብዳቤ ሚጻፋቸውንና በግልባጭም ለኢፊድሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ለአቶ ማለስ ዜናዊ ያሳወቁ ማሆናቸውን ገልጸዋል፡፡** በቀጣይም ለተለያዩ አገሮች **አምባሳደሮች፣ ለኢትዮጥያን ፓርትነርስ ግሩፕ፣ ለሰብአዊ መብት ተሚጋቾች እና ለሌሎችም አካላት ጉዳዩን በማሳወቅ ጩኸታቸውን የሚያሰሙ ማሆናቸውን ገልጸዋል፡፡**

ገዥው ፓርቲ ለጥያቄያቸው ሚልስ የማይሰጣቸው ከሆነ ፍጹም ሰላማዊና ህጋዊ በሆነ መንገድ የረሃብ አድማ ሚድረግ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማካሄድና የመሳሰሉትን በሚድረግ ተቃወሞአቸውን የሚያሰሙ ማሆናቸውን አሳውቀዋል፡፡ ለምናስተላልፈው የትግል ጥሪም የኢትዮጵያ ህዝብ ከጎናችን እንዲቆም በትግሉ በተሰው ሰሚዕታት ስም አደራ እንላለን ብለዋል፡፡ የገዥው ፓርቲ የጥቃት ሰለባ የሆናችሁ የመገናኛ ብዙኃን አባላትም እውነታውን በሚጋለጥ ሚያዊ ግዴታቸውን እንድትወጡ ሲሉ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

የመኢአድ አባላትም በጉዳዩ ላይ ሰፊ ወይይት ካካሄዱ በኋላ እጅግ ብዙ ማስዋዕትነት የተከፈለበት ፓርቲ ለተለጣፊ ሲሰጥ ዝም ብለው ሚየት የማይችሉ ማሆናቸውን ገልጸው ሰላማዊ ትግሉን አጠንክረው እንደሚገፉበት ቃል ገብተዋል፡፡

በዕለቱ በተካሄደው ወይይት ላይ በሰሜን አሜሪካ፣ በካናዳ እና በአወሮፓ የሚገኙ የመኢአድ ድጋፍ ሰጭ ማነበር ተወካዮች በቴሌ ኮንፈረንስ አማካኝነት አዲስ አበባ ከሚገኙት የመኢአድ አባላት ጋር ወይይት አካሂደዋል፡፡

አቶ ቢሹ ማሞ የካናዳ የመኢአድ ድጋፍ ሰጭ ሰብሳቢ <<አሁን የፈተና ጊዜ ነው፡፡ ፈተናውን ማለፍ ይኖርብናል፡፡ እኛ በካናዳ የምንኖር የመኢአድ ደጋፊዎች ትናንትም የመኢአድ፣ ዛሬም የመኢአድ፣ ነገም የመኢአድ ደጋፊዎች ሆነን ነው ጩኸታችሁን የምናሰማው፤ መወደቅ መነሳቱን አብረናችሁ ሆነን እስከ ድል ድረስ በጽናት የምንቀጥል ማሆኑን እናረጋግጥላችኋለን በማለት ሚልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

ኗሪነታቸው ለንደን የሆኑት የአወሮፓ የመኢአድ ድጋፍ ሰጭ ማነበር አስተባባሪ የሆኑት ዶ/ር አበበች በላይም <<እየደረሰባችሁ የሉትን ችግሮች ለመወጣት በምታደርጉት ትግል ከጎናችሁ እንቆማለን፡፡ በምታካሂዱት ወይይት ለምትደርሱበት ወሳኔ ሚሉ በሚሉ አብረናችሁ እንደምንቆም ማስተማመኛ እንሰጣችኋለን>> ብለዋል፡፡

ዷሪነታቸውን ሰሜን አሜሪካ ያደረጉት የመኢአድ የቀድሞ ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ አባይነህ ብርሃኑም እንደዚሁ በቴሌ ኮንፈረንስ የድጋፍና የማበረታቻ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡ የአንጋፋው መምህራን ማኅበር ፕሬዚዳንት የነበሩና አሁን ነዋሪነታቸውን በሰሜን አሜሪካ ያደረጉት ዶ/ር ታዬ ወልደሰሚያት ሃሳባቸውን ለተሰብሳቢው ለማካፈል ዝግጁ ቢሆኑም በተፈጠረው የቴክኒክ ችግር ምክንያት ሳያስተላልፉ ቀርተዋል፡፡ በውጭ ሃገር የሚገኙ ሁሉም የመኢአድ ደጋፊዎች ለኢንጂነር ኃይሉ ሰላምና ጤንነትን ተመኝተዋል፡፡

በተያያዥ ሁኔታም በኢትዮጵያ ከደቡብ፣ ከምሥራቅና ከሰሜን ኢትዮጵያ የተለያዩ የዞን ተጠሪዎች አዲስ አበባ ለሚገኙት የመኢአድ ተሰብሳቢዎች አቋማቸውን በስልክ አስታውቀዋል፡፡

የሃረሪ ክልልና የምሥራቅ ሃረርጌ ዞን የመኢአድ ሰብሳቢ አቶ ኃይሉ ሽዋሰገድ፣ በደቡብ ኢትዮጵያ የጎፋ ልዩ ዞን የመኢአድ ምክትል ሰብሳቢ መምህር አየለ ታደለ እና የምስራቅ ጉጃም ዞን የመኢአድ ሰብሳቢ መቶ አለቃ ዮሃንስ አባተ አቋማቸውን በስብሰባው ላይ አስምተዋል፡፡ በዚህ መሠረትም የምርጫ ቦርድን ጣልቃ ገብነት እንደሚቃወሙ፣ በእነ አቶ ማሙሸት በኩል ላይ የተወሰደውን የዲስፕሊን እርምጃ እንደሚደግፉ፣ ለፕሬዚዳንቱ ለኢንጂነር ኃይሉ ድጋፍ ሙሉ ድጋፋቸውን እንደሚሰጡና መኢአድን ከጥፋት ለማዳን ሰላማዊ ትግሉን ማጠናከር እንዳለባቸው በመግለጽ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡

ክቡር ኢንጂነር ኃይሉ ለመኢአድ ጠንክሮ መውጣት አሁንም ፓርቲውን በቅርብ በመከታተል በሚያስፈልገው ሁሉ ጊዜያቸውን፣ ዕውቀታቸውንና ገንዘባቸውን በመስጠት ተግተው እየሠሩና አመራርም እየሰጡ መሆኑ ይታወቃል፡፡